# አገር ማለት

በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራድዮ ጣቢያ የስነጽሑፍ ክፍል የተዘጋጀ

ነሐሴ 21 ቀን 2015 ዓም(27-08-2023)

ለሰው ልጅ መፈጠር ወይም መወለድ አመቺ የሆነ የተፈጥሮ ቦታና ሂደት መኖር ወሳኝ ነው።እንደዓለማችን ብዙ ዓለማት ቢኖሩም ከመሬት ሌላ ለሰው ልጅ መኖር አመቺና ተስማሚ የሆኑ ዓለማት መኖራቸውን እስካሁን የተደረገው ምርምር አላረጋገጠም።ውሃ ባለበት ቦታ ህይወት ይኖራል የሚል ግምት ቢኖርም ለሰው ልጆች መኖር ግን ብቸኛ ምክንያት ሊሆን አይችልም።ለሰው ህይወት አስፈላጊ ከሆኑት ዋናዋናዎቹ ማለትም የአዬር ጸባይና የተፈጥሮ ስጦታዎች ፣የውሃ፣የእጽዋት የመሳሰሉት ሁሉ ተሟልተው መገኘት ወሳኝ ሲሆን እነዚያም የወደፊቱ ባይታወቅም ለጊዜው ያሉት ባለንባት ዓለም ብቻ ነው።

አገራት ከመመሥረታቸው በፊት ዓለም ለብዙ ሚሊዮን ዓመታት ኖራለች።አሁን የምናዬውን የመሬትና የውቅያኖስ ቅርጽና መልክ ሳትይዝ ሰብሰብ ባለና በተያያዘ መሬት ላይ የሰው ልጅ መፈጠሩን የሚያረጋግጠው እንደዘመናችን ውሃ አቋርጦ ለመሄድ የሚያስችል ችሎታና ጥበብ ሳይኖር ከደቡባዊ የዓለም ክፍል ወደ ሰሜናዊው፣ከምስራቁም ወደምዕራቡ እግሩ እንደመራውና እንዳደረሰው ሄዶ ኑሮ መጀመሩ ነው።ይህ ማለት የሰው ልጅ ሲፈጠር በአገር ደረጃ በተመሠረተ መሬት ላይ እንዳልሆነ ነው።አገር ከብዙ ሚሊዮን ዓመት በኋላ የሰው ልጅ እድገቱን ተከትሎ የፈጠረው የተደራጀ ያኗኗር ዘዴ ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም።

የሰው ልጅ እግሩ እንዳደረሰው ሲጓዝና እንደ አውሬ በዋሻ ውስጥ እዬኖረ በከባቢው የሚያገኘውን የተፈጥሮ ፍራፍሬ እዬለቀመ ከመመገብ አልፎ በቡድን በዘላንነት (Nomadic life) ድንበር ሳያግደው ሲኖር የነበረባት ዓለም በጊዜ ሂደት ቤተሰብ መስርቶ ከምርት ጋር የተያያዘ የሰከነ ኑሮ (satteled life) ለመኖር ቻለ።በዚህም ከመበታተን ይልቅ ሰብሰብ ብሎ መኖሩ የሚሰጠውን ጥቅም በመረዳት የጋርዮሽ ኑሮና ስርዓት(Communual life) ለመገንባት ሁኔታው አስገደደው።እያለ እያለ ከዋሻ ወጥቶ ተራርቀው በተሠሩ የጎጆ መኖሪያ ሠፈሮች መኖር ጀመረ።ተበታትኖ ይኖር የነበረው የሰው መንጋ ኑሮውን ለመምራት፣ እዬጨመረ የመጣውን ፍላጎቱን ለማሟላት ሲል በተለያዩ ምርቶች ላይ ተሰማራ።ከራሱ ፍጆታ አልፎ ትርፍ ምርቱን ይዞ የሌለውን ለማግኘት ከጎረቤቱ ጋር በመለዋወጥ፣የዕቃ በዕቃ ግዢ (Exchange of goods or barter economy)ለተባለው ገበያ መነሻ ሆነ።ይህም የግንኙነቱን ሰንሰለት አጠበቀው።ለገበያ የወጣው ማህበረሰብ ባህሉን፣እምነቱን፣ቋንቋውን ከመጋራቱም ባለፈ የኑሮ በመላመድ ጓደኛ ለመሆን በቃ፣ በመዋለድና በመባዛት፣አንዱ ከሌላው ጋር የደምና የሥጋ ትስስር ፈጠረ።እዬተባዛ ሲመጣና ያለበት መሬት ሲጠበው የግድ ሌላውን አካባቢ ለመቆጣጠርና ይዞታውን ለማስፋት ተገደደ።በዚህ እንቅስቃሴው የግል ይዞታ(Private ownership) ከፈጠረው ግብግብ ውስጥ ገባ።ግጭቱ አንድ ጊዜ በእርቅና በመግባባት ሌላ ጊዜ በማሸነፍና በመሸነፍ ሊወገድ ችሏል።ከመጋጨት ይልቅ በአንድነት መቆሙ እንደሚሻል በተገነዘቡት የማህበረሰቡ ሽማግሌዎች፣ብልሆችና አስተዋዮች ፣ምክርና ጥረት በፈቃደኛነት ወይም በአንዱ ማህበረሰብ አስተባባሪነት ለመቀላቀልና ለመዋሃድ ፣በኋላም ላይ አገር የተባለውን የጋራ ይዞታ ለመመሥረት ቻሉ።ያች ለሁሉም የሁሉም የሆነችው ዓለም(ምድር) ተከፋፍላ የሰዎች የግል ይዞታ በመሆን አገራት ለመፈጠር ቻሉ።አሁን አገራት ላሉበት ደረጃ ለመድረስ የበቁት በዚህ የረጅም ጊዜ ሂደት ነው።በዘመናችን መለኪያ አገር ማለት የመሬት አካል የሆነ ፣በሰዎች አሰፋፈርና ፍላጎት ስም ወጥቶለት፣ያስተዳደር ሰንሰለት ደምብና ሕግ ኖሮት በአንድ ማእከላዊ አስተዳደር ወይም መንግሥት ስር የዋለ የተሰባሰበ ምድር ማለት ነው። አገር የመልክአ-ምድር ውህደት ብቻም ሳይሆን የሰዎች የባህል፣የቋንቋ፣የእምነት፣የምጣኔ ሃብት፣የብዙ ሰብአዊ ተውፊቶች ውህደት ማለት ነው።እነዚህም ብቻ አይደሉም በአገር ደረጃ የከባቢንና የኗሪውን ሕዝብ

እድገት፣ደህንነት፣ አንድነትና ሰላም የሚያረጋግጡ ከአስተዳደር(ፖለቲካው) የሥልጣን እርከን ጀምሮ የሚዘረጉ ተቋማት የመከላከያ፣የጤና፣የትምህርትና ምርምር፣የእርሻ፣የውሃና የሃይል ማመንጫ፣ የእንዱስትሪ ፣ለአካላዊና አይምሮአዊ እድገት የሚረዱ መስኮች መስፋፋት ዋናዋናዎቹ ናቸው።ምንም እንኳን አንዱ ከሌላው የመቅደም ዕድል ቢኖረውም አገር ካለእነዚህ ተቋማት አገር ሊባል አይችልም።

አገር በሂደት በአንድ ከባቢ የሰው ልጅ ተወልዶ ሲቦርቅና ሲሮጥ ያደገበት፣ለቁምነገር የበቃበት፣፣ከሌላው ጋር በብዙ መስተጋብር ተሳስሮ ክፉና ደጉን ተካፍሎ የኖረበት፣ከከባቢው ጋር ተመሳስሎና ፣ያለውን፣ ሰጥቶና የሌለውን ተቀብሎ፣ ባሕልና ቋንቋው ተከብሮለትና፣የሌሎቹንም አክብሮ ፣ የሚፈልገውን እምነት ተከትሎ በነጻነት የኖረበት ከትውልድ ወደትውልድ እዬተቀባበለ የሚረከበውና የሚያስረክበው የጋራ ንብረት ማለት ነው።የሰው ልጅ ሲወለድ እዚህ ቦታ ወይም ከዚህ ማህበረሰብ፣አለያም ከዚህ ቋንቋና ባህል እንዲሁም ሃይማኖት ተከታይ ልወለድ ብሎ መርጦ አይፈጠርም።ሲወለድ ሁሉም የሰው ልጅ ነጻ አይምሮና እርቃኑን የተወለደ፣መተንፈስና የራሱ የሆነ እንቅስቃሴና ድምጽ ያለው ግን ምንም የማይናገር ሆኖ ነው። እስከተወሰነ ድረስም በዚያው የራሱ ማንነት ይኖራል።ከማህጸን ወጥቶ ወደ ገሃዱ ዓለም ሲመጣ ከከባቢው አዬር ጋር ይገናኛል፣ከአቅራቢያ ካሉት ሰዎች በተለይም ከወላጅ እናቱ ጋር በጡትና በጣት በኩል ግንኙነት ያደርጋል።ከከባቢው ድምጽ ጋር ይተዋወቃል።እያለ እያለ ዕድሜው እዬጨመረ ሲሄድ ከከባቢው ጋር እዬተላመደ ሲመጣና ከሰዎች ጋር ካለው ቅርበት የከባቢውን ነዋሪ እዬለመደና እዬመሰለ ይመጣል። በመጀመሪያ የጠበቀ ግንኙነት የሚኖረው ከወለዱትና ከሚንከባከቡት ሰዎች ጋር ነው።በዚህ አባቱንና እናቱን ቀሪ ዘመዶቹንም እዬለዬና እያወቀ ይመጣል። ከመዳህ አልፎ መራመድና መሮጥ ሲጀምር ከቤት ውጭ ከሚኖረው ጎረቤትና ማህበረሰብ ጋር በመገናኘት ከከባቢው ጋር ይለማመዳል።ያንንም ተከትሎ በአካል ማወቅ ብቻም ሳይሆን የከባቢው ሕዝብ የሚከተለውን ሃይማኖት፣የሚናገረውን ቋንቋ፣ የሚያከብረውን ባሕልና ወግ፣ስርዓትና ስነምግባር እዬቀዳ እራሱን ያዋህዳል።

ከሰው ልጅነት ሌላ ምንም አይነት ማንነት ይዞ ያልተፈጠረው ህጻን ባለፋቸው የዕድሜ እርከኖች ብዙ ነገሮችን እዬቀሰመ በመጥፎም ሆነ በመልካም የህይወት መንገድ ያልፋል።ሰዎች የሚፈጥሩትን ችግርና መከራን ወይም መልካም ነገሮችን ይጋራል።ተወልዶ ያደገበት ማህበረሰብ ነጸብራቅ ነው።ለከባቢውና ለማህበረሰብ የሚበጅ ነገር በመሥራትና በተቃራኒው ማህበረሰብን የሚጎዳ ተግባር በማከናወን ላይ ይሰማራል።የቀና ሰዎችና የፈላስፋዎች መኖርና ጥቅም የሚታዬው በዚህ ወቅት ነው። ተወልዶ በማህበረሰብ ሰልፍ ውስጥ የሚገባውን ታዳጊ መክሮና አስተምሮ ከመጥፎ መንገድ ለማውጣት የወላጆች ብቻ ሳይሆን ከማህበረሰቡ ውስጥ ብቅ የሚሉ ፈላስፋዎችና ቀና አሳቢዎች መኖር ወሳኝ ነው።ለህጻኑ አስተሳሰብ ምሳሌና ምልክት የሚሆኑት እኩዮቹ ወይም ታላላቆቹ ናቸው።ከሁሉም በላይ ግን በአገር ላይ የሰፈነው ሥርዓት ለትውልዱ ማንነት ወሳኝና ተጠያቂ ነው።

ሕዝብን (አገርን) ለመምራትና ትውልድን ለማነጽ፣ የአገርን አንድነትና እድገት ለማጽናት፣ወይም ማህበረሰቡን ለማለያዬትና አገር ለመበታተን መንግሥት የተባለ አካል የሚፈጠረው ካለው የማህበረሰብ እይታና አመለካከትና ፍላጎት አንጻር ነው።ከሰማይ አይወርድም።በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ ልማዶችና ፍላጎቶች መካከል አንደኛው ጎልቶ ከወጣ ጉልበት ያገኝና ያንን የሚያንጸባርቅና የሚንከባከብ መንግሥት ይወልዳል።በማህበረሰቡ ውስጥ ጎሰኝነት፣ወይም አክራሪነት፣አገር ወዳድ ወይም ጸረ አንድነት አስተሳሰብ ከነገሠ ያንን ተገን በማድረግ አንዱ በጉልበትም ሆነ በአደረጃጀት የላቀ አካል ወይም ግለሰብም ሆነ ቡድን ሥልጣን ላይ ይወጣና ያሻውን ያደርጋል ማለት ነው።

ዓለም ስትፈጠር አገር ሆና አልተፈጠረችም።በመሸንሸንና በስርዓት አገር እንድትሆን ያደረጋት የሰው ልጅ ነው።ዓለምን ወይም ምድርን አምላክ ፈጠረ፤አገራትን ደግሞ ሕዝብ ፈጠረ ማለት ነው።የሰው ልጅ ለመኖር እንቅስቃሴ ማድረግ ሲጀምር ወደፈለገበት ቦታ የመንቀሳቀስ ልማድን አካብቶ በደረሰበትና ይስማማኛል ባለው መሬት ላይ ለመስፈር ችሏል።በተዘበራረቀና በመንጋ ደረጃ የሰፈረ የሰው ልጅ እራሱን

ከተፈጥሮ አደጋና ከእርስ በርሱ የጥቅም ግጭት ለመዳን ሲል የሰፈረበትን መሬት በመቆጣጠር እድገቱን ተከትሎ አገር አደረገ።

አገር ማለት ቋንቋ ፣እምነት ወይም ባሕል ማለት አይደለም።አገር ማለት እነዚህንና ሌሎቹንም የተለያዩ መስተጋብሮችን የሚያንጸባርቅ ሕዝብ በጋራ የሚኖርበት መሬት ማለት ነው።የሃይማኖትን ነገር እንደምሳሌ ብንወስድ በዬአገሩ ብዙ ተመሳሳይ ሃይማኖቶች የሚከተሉ ሰዎች ይኖራሉ።ይህ ማለት ግን እነዚያ የአንድ ሃይማኖት ተከታዮች ሁሉ የአንድ አገር ዜጎች ናቸው ማለት አይደለም።ሙስሊም ሁሉ የሳውዲ ዜጋ፣ ካቶሊክ ሁሉ ጣልያናዊ፣ፕሮቴስታንት ሁሉ ጀርመናዊ ወይም የሌላ አገር ዜጋ ፣ የአይሁድ ሃይማኖት ተከታይ ሁሉ እስራኤላዊ---ወዘተ፣ እንደማይሆነው ሁሉ እንግሊዝኛ ተናጋሪ እንግሊዛዊ፣ፈረንሳይ ተናጋሪም ፈረንሳዊ---ወዘተ ማለት አይደለም። እነዚህ በተለያዩ አገሮች የሚኖረው የዓለም ሕዝብ በመቀራረብና ፈቅዶም ሆነ ተገዶ የሚይዛቸው የጋራ ተውፌኮች ናቸው።

አገር ማለት በአጭሩ አንድ አካባቢ በሰው ልጆች ፍላጎትና የጋራ ጥረት ለመኖር እንዲያመች ሆኖ የተያዘ መሬት ማለት ነው።ይህንን የጋራ ይዞታ ከወራሪና ከቀማኛ ለመከላከል ሕዝቡ በጋራ ይቆማል፣አስፈላጊ የሆኑትን ተቋማትም እንደ መከላከያ ያሉትን ይገነባል።ለኑሮው የተለያዩ የኤኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ያከናውናል።ለመንፈሳዊና ለአካላዊ ፍላጎቶቹ የተለያዩ ተቋማትን ይገነባል።በዚህ የጋራ እንቅስቃሴው የሚግባባበት የጋራ ቋንቋ ያዳብራል።ባሕልና ተመክሮ እዬተጋራ፣ለሚገጥሙት የተፈጥሮና የውስጥ ችግሮቹ መፍቻ የሚሆኑ መንገዶችንና እውቀቶችን እያጎለበተ በምርምር ልቆ ይሄዳል።አሁን አደጉ ተብለው የሚጠሩ አገሮች ያለፉት በዚህ አቅጣጫ ነው።ሲወለዱ ይዘውት የመጡት የተለዬ የፈጣሪ ስጦታ የላቸውም።

እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ የበቁት አልጋ ባልጋ በሆነ አመችና ቀላል ጉዞ ሳይሆን እልህ አስጨራሽ ትግልና መስዋእትነት ከፍለው ነው።በሃይማኖትና በጎሳ ችግር ሲገጥማቸው ተጋጭተውና ተዋግተው፣ወራሪና አጥፊ ጠላት ሲመጣባቸው በህብረት በመቆምና በጦር ሜዳ ተሰልፎ በማሸነፍ፣የአንድ አገር ባለቤት ለመሆን በቅተዋል።ለዚያ ያልታደሉት ደግሞ የነበሩበትን አገር አጥተው፣ ጠፍተውና ተበትነው ወይም በቅኝ ግዛትነት ወራሪውን ሆነው ለመኖር ተገደዋል።በሁሉም ዘርፍ የፈላስፎችና የቀና ልብ ባለቤት የሆኑ ሰዎች መኖር ወሳኝ ነው።በአንድ ሰው ወይም በተወሰኑ ከይሲ ሰዎች ምክንያት መጥፋት እንዳለ ሁሉ በአንድ ሰው ወይም በተወሰኑ ቀና ሰዎች መኖርም መዳን አለ።ወሳኙ ሌላውን የሚያሳምን ሆኖ መገኘት ነው። ለሰው ልጆች ሁሉ ሰላም፣ በጎና መልካም የሚያስብ ምንም አስቸጋሪ ሁኔታ ቢገጥመውም መልካም ነገር ከሱ ጋር ነችና የማታ ማታ ማሸነፉ አይቀርም።የሰው ልጅ በተፈጥሮው የአብሮነት ፍላጎት እንጂ እንደ አውሬ ተነጥሎ ለብቻው መኖርን አይፈቅድም።ለዚያም ነው ማህበራዊ እንስሳ ወይም( Social Animal) የሚባለው።

ከሰው ልጅ አፈጣጠር ጀምሮ ከሞላ ጎደል ስለአገርና ሕዝብ ከዚህ በላይ ያለውን አጭር ትንታኔ ለማቅረብ ያስገደደን የአገራችን የኢትዮጵያ ጉዳይ ስላሳሰበንና መፍትሔ ለማግኘት ካለን ጉጉት በመነሳት ነው። ኢትዮጵያ እንደሌሎቹ አገሮች በነዋሪዎቿ ጥረት አገር ሆና የኖረች አገር ነች።ልጆቿ በእኩልነት እራቁታቸውን ተወልደው ሰው ሆነው የተፈጠሩና በዕድሜ ከቤተሰብና ከከባቢው ቋንቋ፣ባሕል፣እምነትና ማንነት የወረሱ ናቸው።ሲሞቱም እንደዚያው ባዶ እጃቸውን መቃብር ጉድጓድ ውስጥ ይገባሉ፤ከቶም ቢሆን በህይወት በኖሩበት ዘመን ሰርተው ያፈሩትን ፣ወይም በሃይላቸውና በሥልጣናቸው ቀምተው የሰበሰቡትን ንብረትና ሃብት ይዘው አይሄዱም። ከተወለዱበት ጊዜ የሚለያቸው ቢኖር በጨርቅ መከፈናቸውና በሳጥን ወይም በሸራ መጠቅለላቸው ነው። ያንንም ቢሆን የሚያገኙት የታደሉት ናቸው አለያ የወደቁበት ሳይታወቅ የአውሬ ቀለብ የመሆን ዕድልም ይገጥማቸዋል።በመሬት ላይ ያገኙትን ሃብት ብቻም ሳይሆን ቋንቋ፣ባሕል፣እምነት ይዘው አይሄዱም።በህይወት ዘመናቸው ሲነታረኩበትና ሲጋጩበት ለመሞትም የዳረጋቸውን ጥላቻ ይዘው አይቀበሩም፤ ከሚጠሉት ጋር ጎን ለጎን ቢቀበሩ ግጭትና ጠብ

ወይም ፍቅር አያሳዩም።ሁሉም በድኖች፣የማይሰሙና የማይለሙ ሙታን ይሆናሉ።ከተወሰነም ጊዜ በኋላ በስብሰው አፈርና ትቢያ ይሆናሉ።ከመቃብር በላይ የሚኖረው ማስታወሻቸው የፈጸሙት መልካምና መጥፎ ሥራ ይሆናል።

ዓለም ወይም የምንኖርባት አገር እንደ ትውልዱ ፍላጎት መልኳን እዬለወጠች ትሄዳለች እንጂ አትጠፋም። ምናልባት ብትጠፋ በተፈጠረችበት መልኩ በሚከሰት ውስጣዊና ውጫዊ  ለውጥ ሊሆን ይችላል።ጥቂቶች የሚያደርጉት የተሳሳተ ውሳኔና እርምጃ ብሎም ከልክ ያለፈ ስግብግብነት የፈጠሩት ግጭትና ጦርነት የሚጠቀሙበት አውዳሚ መሳሪያ  ከሚገለው የሕዝብ ቁጥር ጋር በተጨማሪ  የተሠሩትን መልካም ሥራዎችና የእድገት ደረጃዎች ሊያናጋና ሊያፈርስ ይችላል።የከባቢን ገጽታም ሊቀይርና ሊያወድም ይችላል።በአንደኛና ሁለተኛ የዓለም ጦርነት ከተባለው ወዲህ በእኛ ዕድሜ በኢራቅ፣በሊቢያ፣በዬመን፣ በሶማሊያ ያዬነው የአገር ውድመትና የሰው ልጆች መከራ ጥቂት ስግብግቦች የፈጠሩት ሲሆን አሁን ዓለምን ያስጨነቀው የሰደድ እሳት ያስከተለው የአዬር መዛባትም  የዚያ አንዱ ውጤት ነው።ሁኔታው ከቀጠለ ምናልባትም ዓለምን  ለሁሉም የሰው ልጅ ሲኦል ያደርጋት እንደሁ እንጂ  ምድራዊ ክብነቷን አይቀይረውም።የሰው ልጅ በቃኝ ብሎ ከተነሳም የጥፋት መንገዱ እስከነአካቴው ይዘጋና ለሁሉም የተመቸች ትሆናለች ማለት ነው።

መጀመሪያና መጨረሻቸው አንድ የሆነው የሰው ልጅ በመሰል ጥቂት ከይሲ የሰው ልጆች ሃሳብና ፍላጎት እዬተነዳ  ይዞት ከመጣውና ከተፈጠረበት የሰውነት ደረጃ ወርዶ የሚኖርባትንን አጭር የሕይወት ዘመን በሃጢያትና በክፋት አጨቅይቶት ያልፋል።፤በታሪክም ሲረገምና ሲወገዝ ይኖራሉ።ወይም ከእሱ አልፎ ተርፎ ሌሎቹን የሚጠቅም ሥራ ሠርቶ በታሪክ የሚመሰገን  ይሆናል።።አገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ እነዚህን ሁለት አይነት ሰዎችን አፍርታለች።በአንዱ ስትጎዳ በአንዱ ስትጠቀም ኖራለች።ለአንድነቷና ለሕዝቡ ሰላም የታከቱ እንዳሉ ሁሉ ለሕዝብ እልቂት፣ለሰላም ማጣትና ለአገር መፍረስና መዳከም የሠሩ ነበሩ፣አሁንም አሉ።ከደረሰባት ቀውስና የሕዝብ ችግር ለመውጣት የግድ የቀና ሰዎችን ህብረትና ድፍረት ይጠይቃል።ሌላውም ለነዚህ አይነቶቹ ሰዎች ድጋፍ እዬሰጠ አብሯቸው ሊቆምና ከይሲዎችን ሊያሶግድ ይገባዋል።ከይሲዎቹ ሌላውን የሚያሳስቱበት መንገድ የተጎዳና የተበደለ፣በማስመሰል ሌላውን መሰል የሰው ልጅ ተጠያቂ በማድረግ ቋንቋን፣ ድህነትን፣እምነትን፣ባህልን፣የከባቢ ስነልቦናን በመጠቀም ነው።ይህ አይነቱ ጠባብና ሰይጣናዊ አስተሳሰብ ከሰው ልጅ አፈጣጠር ጋር ይቃረናል። ህብረተሰብን ያቀጭጫል፣ከዓለም ማህበረሰብ ጋር ያለያያል።የትልቅ አገር ባለቤትነትን በጠባብ ሰፈር (መንደር)እስረኛነት ይለውጣል።ወደ መጀመሪያው የዋሻ ወይም የጎጆ ኑሮ ውስጥ ይከታል።በጣም የሚገርመው ግን ከባቢውንና ሕዝቡን ለመከራ የሚዳርጉትና የጠባብ መንደር ባለቤትነትን የሚሰብኩት ጩካኞችና አጭበርባሪዎች ከተወለዱበት ሰፈር ብቻም ሳይሆን ከኖሩበት አገር ወጥተው በበለጸጉ አገሮች ውስጥ ኑሯቸውን የሚመሩ መሆናቸው ነው።እናስብለታለን ከሚሉት ማህበረሰብ በዘረፉት ሃብት በውጭ አገር የተደላደለ ቅንጡ ኑሮ መኖራቸው ነው። በሌሎች ሰዎች አገር ውስጥ የመኖርን ጸጋና መብት እዬተጠቀሙበት የአንድ አገር ዜጋ ግን በራሱ አገር ውስጥ የመኖሩን መብት ይገፉታል።

ኢትዮጵያዊነት ማለት የአንድ ማህበረሰብ ማንነት ማለት አይደለም።አማራነት፣ትግሬነት፣ኦሮሞነት፣ ሲዳማነት---ወዘተ ማለት አይደለም።የሁሉም የጋራ ማንነት ማለት እንጂ!ኢትዮጵያ ማለትም የጋራ አገር ማለት ነው።ከላይ እንዳዬነው አገር ማለት ከቤተሰብ፣ወደ መንደር፣ከመንደር ወደ አካባቢ፣ከአካባቢም ወደ አገርነት አድጎ የመጣ ፣የሕዝብ ትስስር የፈጠረው የጋራ ይዞታ ነው።ይህም አንድነት የፈጠረው ዜግነት ለተሻለ እድገትና ሰላም ፣ሃይልና ምንጭ ነው።ይህንን የእድገትና የሰላም ዋስትና የሆነ አንድነት ለመሰባበርና ለማዳከም የሚሹ የውጭ ሃይሎች ቢመቻቸው በሃይል በመውረር አለያም በውስጡ ችግር በመፍጠር አንድነቱን አናግተው የቆመበትን ኢትዮጵያዊ ማንነቱን አፍርሰው ያላቸውን የተፈጥሮ ሃብት ለመንጠቅ፣ ብትንትኑን ለማውጣት መሣሪያ የሚሆን የአገር ተወላጅ በጥቅም እዬገዙ ጥንት ያለፈበትን መንደርተኝነት ተሸክሞ እርስበርሱ እንዲባላና የነሱ አገልጋይ እንዲሆን ያደርጉታል።በአገራችን በኢትዮጵያም ያዩነውና

የምንቃወመው ይህንኑ እኩይ አገር አጥፊ ሃይል ነው።የወያኔና የኦነግ እንዲሁም የሌሎቹ ጸረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ሃይሎች መነሻና ግባቸው ይኸው ነው።አጥፍቶ መጥፋት!

እነዚህ ክፉዎች የአንድ የተወሰነ አገር ሕዝብ ችግሮች ብቻ ሳይሆኑ የዓለም ችግሮች ናቸው።የሚደጋገፉበት ዓለም አቀፍ ሰንሰለት አላቸው።ትግሉን ዓለም አቀፋዊ የሚያደርገውም ይኸው ነው።እነዚህ እኩይ ፍጡሮች  እስካሉ ድረስ በዬትም ሰላምና ፍቅር፣አንድነትና እድገት አይኖርም።ለዓለም ሰላምና ለሕዝብ አንድነት እነዚህ ሃይሎች መወገድ አለባቸው።አገራት በሕዝባዊ ደንብና ሥርዓት መተዳደር አለባቸው። የአምባገነኖች የለያዩተህ ግዛ ደንብና ሥርዓት ከባለቤቶቹ ጋር አብሯቸው መጥፋት አለበት። ኢትዮጵያን የኢትዮጵያውያን እኩል ንብረት ማድረግ የሚቻለውም በዚህ መልኩና ቅኝት በሚደረግ ትግልና በሚገኘው ውጤት ብቻ ነው።ከአጥፊ ሃይሎች ፣ከባንዳዎች፣ከጸረ ሕዝብና ኢሰብአዊ  ከሆኑት ጋር አብሮ መኖር አይቻልም።መታረቅና መግባባትም  እንዲሁ!

አገራት ይበልጥ እዬተቀራረቡ፣ሕዝባቸው በነጻነት ከአንዱ ቦታ ወደሌላው ቦታ እንዲንቀሳቀስ ብቻም ሳይሆን በነጻነት ሠርቶና ሃብት አፍርቶ፣ከወደደው ጋር ተጋብቶና ተዋልዶ  መኖር እንዲችል ሲያደርጉና ይበልጥም ግንኙነቱ ከህብረት ወደ አንድነት እዬተሸጋገረ ሲመጣ እያዬን የእኛ አገር ምሑር ነኝ ባይ የጎሳ ዲሪቶ እዬጎተተ ሥልጣን ላይ ተቀምጦ አገረቢስ አድርጎን ጥቁር ማቅ ሊያለብሰን  ተግቶ እዬሠራ ይገኛል። ይህንን ሥርዓት ለአንዴና ለሁሌዬው ማሶገድ  የኢትዮጵያውያን ብቻም ሳይሆን የሰው ልጆች ግዴታ ነው።

ዓለም የንጹሃን ዓለም ትሆናለች፣ኢትዮጵያም የኢትዮጵያውያን አገር ሆና ትቀጥላለች!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

## ሃገር

በማህጸን ማሳ በፍቅር ተዘርቶ፣

ከብዙ እረቂቃን አንድ ፍሬ ወጥቶ፣

በምዬ ሰውነት ታቅፎ ተደግፎ፣

ከፉ እንዳያገኘው እንዳይነካው መጥፎ፣

የሰው ልጅ ተጸንሶ፣

ስጋ ቆዳ ለብሶ፣

አጥንቱ ተዋቅሮ፣

በጅማት ተሳስሮ፣

አየርና ምግብ በእትብት ተጋርቶ

ሕያው ነፍስ ዘርቶ፣

አካሉ ተሟልቶ፣

አድጎ ቅርጽ አውጥቶ፣

በናቱ ማህጸን ዘጠኝ ወር ቆይቶ፣

ወደሌላው ዓለም ሲመጣ ለመኖር፣

ለናቱ ማህጸን ምትክ የሚሆነው የሚክሰው ነገር፣

የሚበላው ምግብ የሚጠጣው ውሃ፣የሚስበው አየር፣

ሜዳና ተራራ፣ ሜካና ለም አፈር፣

እጽዋትና ፍሬ፣አሸዋና ድንጋይ፣ወንዝና ሸንተረር፣

ሁሉም ተሟልቶለት ምንም ሳይቸገር፣

የሚያስተናግደው የማህጸን ምትክ የትውልድ ሀገር።

የተፈጥሮን ጸጋ የሚካፈልበት፣

በሰብአዊ ተራ የሚሰለፍበት፣

ቢደላው ባይደላው የሚታፈርበት፣

የሚመሽግበት የሚከበርበት፣

በቀደመው ትውልድ የተዘጋጀለት፣

በሕይወትና በሞት የዘላለም ቤቱ፣

ለሰው አገሩ ነው የተወለደበት፣

ኑረው ያለፉበት እናትና አባቱ፣አያት ቅድመአያቱ።

የባህል የታሪኩ፣

የተግባር መድረኩ፣

ጥሎት በሚሄደው ታሪካዊ አሻራ፣

የሚታወቅበት የትውልዱ ስራ፣

ወይም የሚያሳፍር ወይም የሚያኮራ።

የሰው ማንነቱን፣

ጥፋቱን፣ውድቀቱን፣

እድገቱን ልማቱን፣

መልካምና መጥፎ መለኪያ መለያ፣

አገር መስተዋት ነው የትውልድ ማያ።

አገሬ አዲስ

ጥር14-2002 (23-01-2010)